# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

## ሁለተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት

# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር
## ሁለተኛ ክፍል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ 2015 ዓ.ም

# ማውጫ

መግቢያ
አጠቃላይ አላማ
ምዕራፍ አንድ
ማማተብ ፩
፩.፩ ማማተብ ምንድን ነው? ፪
፩.፪ እንዴት እናማትባለን? ፪
፩.፫ የምናማትብበት ምክንያቶች? ፫
ምዕራፍ ሁለት
ቤተ-ክርስቲያን ፭
፪.፩ ቤተ-ክርስቲያን ለምን እንሄዳለን? ፮
፪.፩.፩ ለጸሎት ፮
፪.፩.፪ ለትምህርት ፰
፪.፩.፫ ለአገልግሎት ፰
፪.፪ ቅዳሴና ቅዱስ ቁርባን ፲
፪.፪.፩ ቅዳሴ ስለማስቀደስ ፲
፪.፪.፪ ከቅዳሴ የሚገኝ በረከት ፲፩
፪.፪.፫ ቅዱስ ቁርባን እንዴት መቁረብ እንዳለብን ፲፪
፪.፪.፬ ከቅዱስ ቁርባን በፊትና በኋላ ማድረግ ያለብንና የሌለብን ፲፪
፪.፫ ስለ ቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት ፲፬
ምዕራፍ ሦስት
ትሕትና ፲፭
፫.፩ ትሑት መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ፲፮
፫.፪ ትሑት መሆን ያለብን ለማን ነው? ፲፮
፫.፫ በመጽሐፍ ቅዱስ የትሕትና ምሳሌዎች ፲፮
ምዕራፍ አራት
ሥርዓትን ማክበር ፲፱
፬.፩ ሥርዓት ማክበር በቤት ውስጥ ፳
፬.፪ ሥርዓት ማክበር በአካባቢ ፳

፬.፫ ሥርዓት ማክበር በትምህርት ቤት ፳

፬.፬ ሥርዓት ማክበር በቤተ ክርስቲያን ፳

፬.፭ ሥርዓት ማክበር በማንኛውም ቦታ ፳፩

ምዕራፍ አምስት

ሰውን ሁሉ መውደድ ፳፫

፭.፩ ሰውን ሁሉ መውደድ ማለት ምን ማለት ነው? ፳፬

፭.፪ ጠላታችን ማን ነው? ፳፬

፭.፫ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ማለት ምን ማለት ነው? ፳፬

ዋቢ መጻሕፍት ፳፭

## መግቢያ

የክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ምን እንደሆነ በ፩ኛ ክፍል ትምህርታችሁ ተምራችኋል በ፪ኛ ክፍል ሥነ-ምግባር ትምህርታችን ውስጥ ደግሞ አምስት ምዕራፎች ይገኛሉ ። በየምዕራፍ ያሉትን ትምህርቶች ተምረን፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ጠብቀን፣ በትሕትና ኖረን፣ በምግባር እግዚአብሔርን፣ ቤተሰቦቻችንን አስደስተን ለቤተ ክርስቲያን ምርጥ ልጆቿ ሆነን እንድንኖር እግዚአብሔር ይርዳን።

## አጠቃላይ አላማ

በዚህ ክፍል ትምህርታቸውን የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርቱን ተምረው ሲጨርሱ፦

- የማማተብን ሥርዓት ጠንቅቀው ያውቃሉ።
- በቤተ ክርስቲያን የሚካሄዱትን ሥርዓቶች ጠንቅቀው ያውቃሉ።
- የጸሎትን ጥቅም ይረዳሉ።
- በትሕትና ዝቅ ብሎ መኖርን ይለምዳሉ።
- ሰውን ሁሉ እኩል መውደድ እና ማክበር እንዳለባቸው ይረዳሉ።

# ምዕራፍ አንድ
# ማማተብ

### የምዕራፉ ዓላማ

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- ስለ ማማተብ ክርስትያናዊ ትርጉም ያውቃሉ፣
- እንዴት ማማተብ እንዳለባቸው ይረዳሉ፣
- ማማተብ መቼና በምን ቦታ ላይ መጠቀም እንዳለባቸው ይረዳሉ::

### ቁልፍ ቃላት

- ማማተብ በመስቀል አምሳያ ሰውነታችንን መባረክ ነው::
- ቤተ ክርስቲያን ማለት የክርስቲያኖች ቤት ናት::

### የማስጀመሪያ ጥያቄዎች


- ልጆች  ማማተብ ምንድነው?
- ስታማትቡ እጃቻችሁን እንዴት እንደምታደርጉ አሳዩ?
- የምታማትቡት መቼ ነው ምን እያላችሁ ታማትባላችሁ?

## ፩.፩ ማማተብ ምንድን ነው?

ልጆች ማማተብ ማለት የቀኝ እጅ ጣቶቻችንን በማመሳቀል ከላይ ወደታች ከግራ ወደቀኝ በማንቀሳቀስ ሰውነት ላይ የመስቀል ምልክት መሥራት ማለት ነው::

## ፩.፪ ማማተብ ምንድን ነው?

ስናማትብ በመጀመሪያ ጣቶቻችንን በመስቀል አምሳል ማድረግ አለብን(አመልካች ጣትን ቀጥ በማድረግ፣አውራ ጣትን ከአመልካች ጣት ስር በማስጎንበስ የመሀል ጣትን በአመልካች ጣት መሀል ላይ አግድም በማሻገር) :: በመቀጠል በመስቀል አምሳል ቅርጽ ያደረግነውን ጣታችንን ግንባራችንን አስነክተን ወደ ደረታችን በመውሰድ ከደረታችን ደግሞ ወደ ግራ ትከሻችን (የሰውነታችን ክፍል) መውሰድ በመጨረሻ ወደ ቀኝ ትከሻችን እጃችንን በመውሰድ ማማተብ እንጨርሳለን:: የዚህም ከላይ ወደ ታች ማማተባችን ትርጉም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን የሚያሳስብ ሲሆን ከግራ ወደቀኝ ማማተባችን ደግሞ ግራ የሲኦል ምሳሌ ስለሆነ በሲኦል የነበሩትን ነፍሳት ወደ ገነት የማስገባቱ ምሳሌ ነው::



ሥዕል ፩ በትዕምርተ መስቀል የሚያማትብ ልጅ

## ፩.፫ የምናማትብበት ምክንያቶች?

ልጆች የምናማትብባቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

- ጸሎት ስንጀምር እና ስንጨርስ
- የምንመገበውን ምግብ መብላት ስንጀምር እና ስንጨርስ
- ሥራዎቻችንን መሥራት ስንጀምር ስንጨርስ
- ጌታችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገልንን ውለታ ለማስታወስ
- ሰይጣንን ለማባረር

ልጆች በጸሎት ጊዜ የማማተብ አስፈላጊነቱ፡

- በጸሎት ጊዜ ኀሊናን የሚዋጋ ክፉ መንፈስን ፣ አጋንንትን ለማባረር
- የዓለም መድኅን የኢየሱስ ክርስቶስን መውረድ መወለድን ለመግለጥ
- ነገረ መስቀሉና፡- አምላክ በመስቀሉ የፈጸመውን የድህነት ሥራ ለማሰብ
- በግራ /በኃጢአት/ ወድቀን የነበርነውን ወደ ቀኝ /ወደ ጽድቅ/ እንደመለሰን ፣ ከሞት ወደ ሕይወት ከሲኦል ወደ ገነት እንደተሻገርን ለማረጋገጥ ነው።

በትዕምርተ መስቀል የሚያማትቡባቸውም ጊዜያት፡-

- ጸሎት ሲጀመር ፣
- በጸሎት ውስጥ መስቀልን የሚያነሳ ቃል ሲኖር ፣
- በጸሎቱ መካከል ኀሊናን የሚያውክ ክፉ ሐሳብ ሲያጋጥም፣
- በትምህርት ቤት ፈተና ስንጀምር እንዲሁም ፣
- ማዕድ ስንባርክ እና የመሳሰሉትን ስናደርግ በትዕምርተ መስቀል እናማትባለን።

## መልመጃ ሀ

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።

፩. ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ ማማተብ ይኖርብናል።

፪. ለአገልግሎት ስንቆም ማማተብ አለብን።

፫. ምግብ ልንመገብ ስንል ማማተብ የለብንም።


# ምዕራፍ ሁለት
# ቤተ-ክርስቲያን

ቤተ - ክርስቲያን የክርስቲያኖች መሰብሰቢያ ቅዱስ ቦታ ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች (ከመኖሪያ ቤታችን እንዲሁም ከሌሎች ቤቶች) ይለያል። ምክንያቱ፤-

- ለእግዚአብሔር ሥርዓተ አምልኮ የምንፈጽምበት ቦታ ስለሆነ
- የቅድስና ሥራ የሚሠራበት ቦታ ስለሆነ

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

- ቤተ-ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?
- በቤተ-ክርስቲያን ምን ምን ሥርዓት ይፈጸማል?
- ቤተ-ክርስቲያን በማን ትመሰላለች?




ሥዕል ፩ ፡ ቤተ ክርስቲያን

# ፪.፩ ቤተ-ክርስቲያን ለምን እንሄዳለን?

ልጆች ዛሬ የምንማረው ስለ ቤተ-ክርስቲያን ነው።
ቤተ-ክርስቲያን ማለት የክርስቲያኖች ቤት ማለት ነው። ቤተ-ክርስትያን የምንሄደው ጌታ እግዚአብሔር በወንጌል << ሁለትም ሦስትም ሆናችሁ ብትሰበሰቡ እኔ በመካከላችሁ እገኛለሁ>> ባለው ቃል መሠረት ከክርስቲያኖች ጋር ሆነን የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር ፣ ለመዘመር ፣ ለመጸለይ ፣ ቅዳሴ ለማስቀደስ እና ለመቀደስ ፣ ለመቁረብ ፣ ከአባቶች በረከት ለመቀበል ፣ ቤተክርስቲያን እንሔዳለን። በተጨማሪም ቤተክርስቲያን ለምን እንደምንሄድ በዝርዝር ከዚህ በታች እንመለከታለን።

## ፪.፩.፩ ለጸሎት

ልጆች ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደሆነ አንደኛ ክፍል ትምህርታችሁ ላይ ተምራችኋል። ስለዚህ ቤተ-ክርስቲያን እግዚአብሔርን በጸሎት ለማነጋገር እንሄዳለን ። እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ የሚገኝ ቢሆንም በተለየ ሁኔታ የሚገኝበት ስፍራ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ ጸሎታችንን በቤተክርስቲያን እናደርጋለን።



ሥዕል ፫ ፡ ለጸሎት የቆሙ ሕፃናት

### ፪.፩.፪ ለትምህርት

ክርስቲያኖች ለትምህርት ወደ ቤተ-ክርስቲያን እንሄዳለን የምንማረውም የእግዚአብሔርን ቃል ነው:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ለነፍሳችን ምግብ ስለሆነ ለሥጋችን እንጀራን፣ እንደምንመገበው ሁሉ ለነፍሳችንም የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልጋታልና ቃለ እግዚአብሔርን ቤተ-ክርስቲያን ሄዶ መማር ያስፈልጋል:: ሰው በእንጀራ ብቻ መኖር እንደ ማይችል ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር በማቴዎስ ወንጌል ምዕ ፬ ቁ ፬ ላይ ‹‹ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል›› በማለት ያስተማረን በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ቃሉን መማር ያስፈልገናል:: ስለዚህ ከአባቶች እግር ስር ቁጭ በማለት ቃለ እግዚአብሔርን ልንማር ይገባናል:: በቤተ-ክርስቲያን ትምህርት የሚሰጥባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ በዐውደ ምሕረት (በቤተ መቅደሱ መግቢያ በር ላይ) በንስሓ አባት እና በጽዋ ማኅበራት ሲሆን በእናንተ እድሜ ላሉ አዳጊዎች ግን በዋነኝነት ትምህርት የሚሰጠው በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ነው::

### ፪.፩.፫ ለአገልግሎት

- ስለ አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱስ ‘… ልጆች ሆይ በፊቱ ትቆሙና ታገለግሉት ዘንድ አገልጋዮቹም ትሆኑ ዘንድ ታጥኑለትም ዘንድ እግዚአብሔር መርጧችኋልና ቸል አትበሉ” ፪ኛ ዜና ፳፱:፩-፲፩
- አገልግሎት ማለት የሰሙትንና ያዩትን የእግዚአብሔርን ቸርነት መመስከር፣ ያወቁትን መንፈሳዊ ዕውቀት ላላወቁት ማሳወቅ እንዲሁም በተለያዩ መንፈሳዊ ሥራ ማለትም በመዝሙር፣ በትምህርት፣ በቅዳሴ እና በመሳሰሉት መሳተፍ ማለት ነው:: በአጠቃላይ በቤተክርስቲያን የምናደርጋቸው ነገሮች በሙሉ ከእግዚአብሔር ዋጋ የምንቀበልበት እስከሆነ ድረስ አገልግሎት ይባላሉ::
- ልጆች ወደ ቤተ-ክርስቲያን የምንሄደው ለማገልገል እስከሆነ ድረስ በመጀመሪያ ማንን እንደምናገለግል እና እንዴት ማገልገል እንዳለብን ልናውቅ ይገባናል::
- ማንን እንደምናገለግል ማወቅ
- ከላይ ባየነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ካሉ ወንድሞች እና እህቶች መካከል መርጦ በዚህ በተቀደሰው ስፍራ የሰበሰበን እንድናመሰግነውና እንድናገለግለው ነው::
- አንድ አገልጋይ የሚያገለግለው ማንን እንደሆነ ካልተረዳ ቸልተኛ ይሆናል አገልግሎቱን

ይረሣል ወይም ይታበያል። ስለዚህ የምናገለግለው እግዚአብሔርን እንደሆነ በማወቅ ተጠንቅቀን ልናገለግል ይገባናል።



ሥዕል ፬ ፡ በዝማሬ የሚያገለግል ሕፃን

## ፪.፪ ቅዳሴና ቅዱስ ቊርባን

ልጆች ከወላጆቻችሁ ጋር ቅዳሴ መጥታችሁ ታውቃላችሁ?

ቅዳሴ ትልቅ በረከት የሚገኝበት አገልግሎት ነው።

ልጆች ቅዳሴ ምንድን ነው?




ሥዕል ፫ ፡ በሥርዓተ ቅዳሴ ወንጌል ሲነበብ

### ፪.፪.፩ ቅዳሴ ለማስቀደስ

ልጆች ቅዳሴ ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበት ሰዎች እና መላእክት በእግዚአብሔር ፊት ለምስጋና ለአምልኮ አብረው የሚቆሙበት መንፈስቅዱስ የሚወርድበት ትልቅ በረከት የሚያስገኝ የቤተ-ክርስትያናችን ጸሎት ነው። ቅዳሴ ማስቀደስ ማለት ከዚህ ታላቅ በረከት ለመሳተፍ በቦታው እና በሰዓቱ መገኘት ማለት ነው። ልጆች በቅዳሴ የካህናት አባቶች የአገልግሎት ድርሻ አለ የምእመናን ድርሻ አለ የእግዚአብሔር ድርሻ አለ። ስለዚህ እኛ የሚጠበቅብን ተሰጥዖ በመቀበል ማስቀደስ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ በበረከት ይባርከናል።

### ፪.፪.፪ ከቅዳሴ የሚገኝ በረከት

ልጆች ከላይ እንዳየነው ቅዳሴ ሰዎችና መላእክት አንድ ላይ ለጸሎት ለምስጋና ለአምልኮ የሚቆሙበት ሥርዓት ስለሆነ እግዚአብሔር በቅዳሴው ላይ ተገኝቶ አገልጋዮቹንም ምእመናኑንም ይባርካል፡፡ ስለዚህ ሁልጊዜ ቅዳሴ ሲቀደስ መንፈስቅዱስ ቁርባኑን ለመባረክ ስለሚመጣ በቅዳሴው የተገኙ ምእመናንም ይባረካሉ ስለዚህ ልጆች ቅዳሴ ማስቀደስ በረከት ስላለው ሁሌም ልናስቀድስ ይገባናል፡፡



ሥዕል ፯ ፡ ቅዳሴ የሚያስቀድስ ሕፃን

### ፪.፪.፫ ቅዱስ ቊርባን እንዴት መቁረብ እንዳለብን

ልጆች ቊርባን መቁረብ ማለት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋ እና ክቡር ደም መቀበል ማለት ነው፡፡ እሱን ስንቀበል ደግሞ ጌታችን ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው ፡፡ ስለዚህ ጌታችንን መቀበል ታላቅ ነገር ስለሆነ እንደ ተራ ምግብ እና መጠጥ ስላልሆነ መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ ቀጥለን እንመለከታን ፡፡

### ፪.፪.፬ ከቅዱስ ቊርባን በፊትና በኋላ ማድረግ ያለብንና የሌለብን

ልጆች ቊርባን ከመቁረባችን በፊት መደረግ ያለባቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተጣላነው ያስቀየምነው ሰው ካለ ይቅርታ ብለን መታረቅ፣
- የወሰድነው የኛ ያልሆነ ነገር ካለ መመለስ፣
- ልብሳችንን እና ሰውነታችንን ማጠብ፣
- ከ ቊርባን በፊት ወላጆቻችን በሚነግሩን መሰረት ከምግብ መከልከል፣
- ለቅዳሴ በጠዋት ስለምንነሳ፤ ማታ በጊዜ መተኛት፣
- በሰዓቱ ወደ ቤተ-ክርስቲያን መሄድ እና ቅዳሴ ከመገባቱ በፊት መድረስ፣
- ቅዳሴውን በሥርዓቱ ቆመን ማስቀደስ፣
- የ ቊርባን ሰዓት ሲደርስ ሰልፍ ይዘን በሥርዓት መቀበል፡፡

ከቆረብን በኋላ የምናደርጋቸው ጥንቃቄዎች

- አፋችንን ምግብ እስክንቀምስ ድረስ መሸፈን፣
- ወሬ አለማውራት፣
- አለመሯሯጥ /አርፎ መቀመጥ/ ፣
- እንዳያስመልሰን በልክ መብላት፣
- እጃችን እና ሰውነታችንን አለመታጠብ፣
- ሰውነታችን መድማት ስለሌለበት ስለት ያለው ነገር አለመንካት፣
- ምራቃችንን አለመትፋት



ሥዕል ፯ ፡ ቅዱስ ቁርባን የተቀበለ ሕፃን

## ፪.፫ ስለቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት

ልጆች ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ብንሆንም ለቤተመቅደሱ አገልግሎት ደግሞ የተመረጡ አገልጋዮች አሉ። የቤተ-ክርስቲያን ካህናት ፤ መሪጌቶች ፤ዲያቆናት ሌሎችም የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሰሩ አገልጋዮች ይባላሉ። ካህናት አባቶች በምድር ላይ የእግዚአብሔር ተወካዮች ስለሆኑ መከበር አለባቸው። ልጆች ከእናንተም መካከል እግዚአብሔርን እንድታገለግሉ የሚመርጣችሁ ትኖራላችሁ። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሰሩ አባቶቻችንን ማክበር እና የሚሉንን ማድረግ መንፈሳዊ ግዴታችን ነው።

ስለ ቤተ-ክርስቲያን እና አገልግሎት የሚያስረዱ ጥቅሶች

የማቴ. ፬ ÷ ፬ ፤ ሉቃ. ፲÷ ፵፪ ፤ ፩ኛ ጴጥ. ፪ ÷ ፳ ፤ ፪ኛ ዜና. ፳፱ ÷ ፩-፲፩

### መልመጃ ለ

### የሚለተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

፩. ቤተ-ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. የመኖሪያ ቤት ነው።

ለ. ትምህርት ቤት ነው።

ሐ. መሥሪያ ቤት ነው።

መ. የአምልኮ ቦታ ነው

፪. ስንቆርብ ከምን ከምን መከልከል አለብን?

ሀ. ውኃ ከመንካት

ለ. ከመሯሯጥ

ሐ. ከመጠን በላየ ከመብላት

መ. ሁሉም መልስ ነው።

፫. አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. በቤተክርስቲያን የሚደረግ ማንኛውም መልካም ተግባር ነው።

ለ. እግዚአብሔርን ማገልገል ነው።

ሐ. ቤተክርስቲያንን ማገልገል ነው።

መ. ሁሉም መልስ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት
# ትሕትና

## የምዕራፉ ዓላማ

### ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ

- ስለ ትሕትናና ሥርዓት ማክበር አስፈላጊነትና ጥቅም ይረዳሉ።
- ትሑት ለመሆን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይረዳሉ።
- ትሑት መሆን ያለባቸው ለምን እንደሆነ ያውቃሉ።

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

- ልጆች ትሕትና ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ?
- ልጆች በመጽሐፍ ቅዱስ የትሕትና ምሳሌ የሆኑ ቅዱሳንን አባቶች እነማን ናቸው?
- ልጆች እናንተስ ትሑት ናችሁ?

## ፫.፩ ትሑት መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

ልጆች ትሑት መሆን ማለት ሁሉ ነገር ኖሮአችሁ እንደሌላችሁ መሆን፤ ሁሉን ነገር ማድረግ እየቻላችሁ እንደማትችሉ መሆን ወይም ደግሞ ራስን ዝቅ አድርጎ መኖር ማለት ነው ::

**በቃል የሚጠና ጥቅስ**

**‹‹እንደወንድሞች ተዋደዱ ሩኅሩሆች እና ትሑታን ሁኑ::››**

**፩ኛ ጴጥ ፫ : ፰**

ለምሳሌ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ሁሉ ፈጣሪ ሲሆን የተወለደው ግን በከብቶች በረት ነው ::በዓለም ላይ ያለው ሀብት ሁሉ የእሱ ሆኖ ሳለ እሱ ግን እንደ ደሀ በበረት ተወለደ::ትሑት ስንሆን ምንም ሀብታም ብንሆን እንኳን እንደጌታችን ራሳችንን ዝቅ አድርገን ደሐ መስለን መታየት እንችላለን ማለት ነው ፣ ምንም ብዙ እውቀት ቢኖረን እኔ አውቃለሁ ብለን እራሳችንን ከፍ ከፍ አለማድረግ ማለት ነው:: የሌለንን ነገር እንዳለን እያስመሰልን በሰዎች ላይ ትዕቢተኛ እና ኩራተኛ መሆን የለብንም::

ትሑታን የምንሆንበት ምክንያት፤ ምንም እንኳን ብዙ ነገር ያለን ቢሆንም ያለን ነገር ከእግዚአብሄር የተሰጠ እና የትኛውም ሰዓት ላይ ሊጠፋ የሚችል ነገር መሆኑን በመረዳት በእርሱ አለመመካት:: ሀብት ንብረት አለኝ ብሎ ትዕቢተኛ አለመሆን ምክንያቱ ሀብቱና ንብረቱ በአንድ ጊዜ ሊጠፉ ይችላሉ እና ነው::

ስለዚህ እያለን የሌለን መሆን ትሕትና ይባላል:: አባችን ኢዮብ እንደ እርሱ ዓይነት ሃብታም አልነበረም ነገር ግን እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ሀብቱን፣ ንብረቱን ልጆቹን ሳይቀር አጣ::

## ፫.፮ ትሑት መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

ትሑት መሆን ያለብን ለሁሉም ሰው ነው። ለታናናሾቻችንም ለታላላቆቻችንም ትሑት መሆን አለብን ፣ ሌሎችን ማስቀደም አለብን። ልጆች የትሕትና በረከትና ክፍያ ከእግዚአብሔር ስለሆነ ለግዜው በሰዎች ፊት የተዋረድን /የተሸነፍን/ ቢመስለንም እግዚአብሔር ግን ይባርከናል።

## ፫.፯ በመጽሐፍ ቅዱስ የትሕትና ምሳሌዎች

ልጆች ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ለትሕትና ምሳሌ የሚሆኑ ቅዱሳን ብዙ ቢሆኑም ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም
- መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ
- ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ

**በቃል የሚጠና ጥቅስ**

‹‹ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና።››

ማቴ ፲፩ ፥ ፳፱

## መልመጃ ሐ

### የሚከተሉትን ጥያቄዎ መልሱ፡፡

፩. ትሑት መሆን ያለብን ለማን ነው?

፪. ትሕትናን ከማን ከማን እንማራለን?

፫. የትሕትና መገለጫው ምንድን ነው?

# ምዕራፍ አራት
# ሥርዓትን ማክበር

## የምዕራፉ ዓላማ

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- በቤታቸው፣ በትምህርት ቤት፣ በቤተ ክርስቲያን እና በየትኛወም ቦታ እንዴት ሥርዓት ማክበር እንዳለባቸው ያውቃሉ።

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

- ልጆች ሥርዓት ማክበር ስንል ምን ማለታችን ነው?
- ልጆች የሥርዓት ባለቤት ማንነው?
- ልጆች ሥርዓት አክባሪዎች መሆንን መቼና የት እንፈጽማለን?

ልጆች ቤተ-ክርስቲያን የሥርዓት ቤት ናት ይህንን ደግሞ የወሰደችው ከፈጣሪዋ ከእግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያደረገው በሥርዓት ነው:: ፀሐይ የምትወጣው በቀን ነው ጨረቃ ደግሞ የምትወጣው በማታ ነው ይህ እግዚአብሔር ነገሮችን በሥርዓት የማድረጉ ምሳሌ ነው::ክረምት ጊዜውን ጠብቆ ይመጣል በጋም እንደዚሁ በሰዓቱ ይመጣል:: ገበሬ ዘር ይዘራል ከዛ ዘሩ ጊዜውን ጠብቆ ይደርሳል ይህን ዘር እንዲደርስ የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ ሁሉም ነገር ሥርዓት ስላለው እኛም የቤተክርስቲያን ልጆች ሁሉን ነገር አባቶቻችንና እናቶቻችን ሲያደርጉ እንደኖሩት በሥርዓት ማድረግ አለብን:: በዚህ ምዕራፍ ስለነዚህ ሥርዓቶች እንማራለን::

## ፬.፩ ሥርዓት ማክበር በቤት ውስጥ

ልጆች በቤት ውስጥ ቤተሰቦቻችሁ ያስቀመጡላችሁ ሥርዓት አለ:: ይህንን ሥርዓት ማክበር አለባችሁ:: ለምሳሌ ቤት እንግዳ መጥቶ አዋቂዎች ወሬ ሲያወሩ ልጆች መስማት ስለሌባቸው ዞር ማለት አለባቸው:: የቤት ሥራ ካላችሁ የቤት ሥራችሁን መሥራት በትምህርት ቀን ቴሌቪዥን አለማየት፣ ልብሶቻችሁን አጣጥፋችሁ ማስቀመጥ፣ ጮክ ብሎ አለማውራት፣ ጨዋታ ስንጫወት ሌሎችን በማይረብሽ ሁኔታ መጫወት፣ ስማችን ተጠርቶ ካልተጠየቅን በቀር በሰዎች ንግግር መሐል ጣልቃ አለመግባት፣ እና ተፈልገን ስንጠራ ደግሞ ቶሎ ብለን አቤት ማለት እንዲሁም ታላላቆቻችን ሲመጡ ከመቀመጫችን ተነስተን ወንበር መልቀቅ ያስፈልጋል::

## ፬.፪ ሥርዓት ማክበር በአካባቢያችን

ልጆች በሰፈራችን ሥርዓትን ማክበር አለብን:: ለትልልቅ ሰዎች በመላክ ፣አካባቢውን ለማያውቁ ሰዎች አቅጣጫ ማሳየት፣ ትልልቅ ሰዎች የያዙትን ዕቃ የምንችለው ከሆን ተቀብለን ማገዝ፣ሰው ቤት ሳንጠራ አለመግባት፣ የሰው በር ሳናንኳኳ አለመግባት እና የመሳሰሉት ሁሉ ከሥርአት ጋራ የሚያያዙ ናቸው:: ተልከን ካልሆነ በቀር መንገድ ለመንገድ መዞር የለብንም:: ይልቁንም ቤታችን ገብተን ማጥናት ወይም ቤተሰቦቻችንን እቤት ውስጥ በሥራ ማገዝ ይገባናል:: ጌታችንም እናቱን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በቤት ውስጥ በሥራ ያግዛት ነበረ::

## ፬.፫ ሥርዓት ማክበር በትምህርት ቤት

ልጆች በትምህርት ቤት ትምህርት ቤቱ ያስቀመጠውን ሥርዓት ማክበር ግዴታ አለብን። በሰዓቱ መድረስ፣ መምህራኖቻችንን፣ተማሪዎችን እና ሌሎች የትምህርት ቤቱ ሠራተኞችን ማክበር፣ የቤት ሥራችንንም ሠርተን መገኘት አለብን። የክፍል ሥራችንን መስራት እና በክፍል ውስጥ አስተማሪ ሲያስተምር መከታተል እንዲሁም ወሬ አለማውራት አንዱ የስነ ሥርአት መገለጫ ነው።

## ፬.፬ ሥርዓት ማክበር በቤተክርስቲያን

ልጆች ቤተክርስቲያን የሥርዓት ቤት ስለሆነች ሁሉም ነገር በሥርዓት መሆን አለበት ። ለምሳሌ ሴቶች መቆም ያለባቸው በሴቶች ቦታ ሲሆን፤ወንዶችም መቆም ያለባቸው በወንዶች ቦታ ነው ፣በካህናት መግቢያ በር ምዕመናን አይገቡም። በቅዳሴ ጊዜ ካህኑ የሚያዜሙትን እና የሚደግሙትን ጸሎት ምዕመናን ከካህኑ ጋር በአንድነት አይሉትም። ምእመናን ራሳቸውን ችለው የሚቀበሉት የቅዳሴ ክፍል ተሰጥኦ ይባላል። ልጆች ቤተክርስቲያን ያስቀመጠችልንን ሥርዓቶች መጠበቅ በረከት ያሰጣልና አድርጉ የምንባለውን ማድረግ አታድርጉ የምንባለውን ደግሞ መተው ያስፈልጋል።

## ፬.፭ ሥርዓት ማክበር በማንኛውም ቦታ

ልጆች ክርስቲያኖች የክርስቶስ ልጆች ስለሆኑ በሔዱበት ቦታ ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያስከበር ሥራ መሥራት ይኖርባቸዋል ። ቤተክርስቲያን ስትመጡ የምታሳዩትን በጎ ምግባር እና ሥርዓት በሁሉም ቦታ ማድረግ አለባችሁ። ልጆች አስታውሱ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ያለ ነው ስለዚህ በሁሉም ቦታ እሱን የሚያስከብር ሥርዓት ሊኖረን ይገባል።

## መልመጃ መ

በ "ሀ" ስር ያሉትን በ"ለ" ስር ከሚገኙት ተስማሚ መልስ ጋር በመስመር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩. ሥርዓት ማክበር | ሀ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ |
| ፪. ሥርዓት የት እናከብራለን | ለ. ሕግን መጠበቅ |
| ፫. የሥርዓት ባለቤት ማነው | ሐ. በሁሉም ቦታ |

# ምዕራፍ አምስት
# ሰውን ሁሉ መውደድ

## የምዕራፉ ዓላማ

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- ሰውን ሁሉ መውደድ እንደሚገባ ይገነዘባሉ፡፡
- ጠላት የሚባለው ማን እንደሆነ ያውቃሉ፡፡
- ጠላትን መውደድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይረዳሉ፡፡

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

- ልጆች ሰውን ሁሉ ትወዳላችሁ?
- ልጆች የማትወዱት ሰው አለ? ለምን ?

## ፳.፩ ሰውን ሁሉ መውደድ ማለት ምን ማለት ነው?

ልጆች እኛ የክርስቶስ ተከታዮች ስለሆንን እሱ ያደረገውን ነገር ማድረግ አለብን ። ከእነዚህ በጣም መልካም ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ ሰውን ሁሉ መውደድ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ሰው ይወዳል ፣ለሁሉም ሰው ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቷል ። የእግዚአብሔር ልጅ የድንግል ማርያም ልጅ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው የተሰቀለው ለሁሉም ሰው ነው /ዮሐንስ ፫፥፲፮/። ሰዎች ባይወዱትም፤ትዕዛዙን ባይጠብቁም እንኳን ይወዳቸዋል ። ስለዚህ እኛም ሰዎችን ሁሉ መውደድ አለብን።

## ፳.፪ ጠላታችን ማን ነው?

ልጆች ጠላታችን ሰይጣን ነው። ጠላት የሆነው ደግሞ ከእግዚአብሔር የሚለየንን ክፉ ሥራ ስለሚያሠራን ነው። እግዚአብሔር የማይወዳቸውን ሥራዎች ለምሳሌ መዋሸት፣መስረቅ፣መሳደብ፣መደባደብ ፣የማይረባ ወሬ ማውራት፣ ጊዜን በከንቱ ማባከን እነዚህ ሁሉ ሰይጣን የሚያሠራን ክፉ ሥራዎች ናቸው። ለዚህ ነው ሰይጣን ጠላታችን ነው የምንለው።

## ፳.፫ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ማለት ምን ማለት ነው?

ልጆች ጠላታችን ሰይጣን ክፉ ነገር የሚያደርግብን በክፉ ሰዎች አድሮ ነው። ስለዚህ እነዚህ ክፉ የሚያደርጉብን ሰዎች ሰይጣን እየተጠቀመባቸው ስለሆነ እነሱን መውደድ እና ሥራቸውን ግን መጥላት አለብን። የሚሰድቡን ፣የሚመቱን ፣ክፉ ወሬ የሚያወሩብን ሰዎችን መጥላት የለብንም እግዚአብሔር ወደ ቀና መንገድ እንዲመራቸው መጸለይ አለብን ። "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል" ያዕ ፬፥፯

## መልመጃ ሠ

### ትክክል የሆኑትን እውነት ወይም ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ።

፩. የሰው ልጅ ጠላቱ ሰይጣን ነው

፪. መልካም ከሆነ ነገር የመጀመሪው ሰውን እንደራሳችን መውደድ ነው

፫. ጠላቶቻችሁን ውደዱ ሲል ክፉ የሚያደርጉባችሁን ውደዱ ማለቱ ነው

## ዋቢ መጻሕፍት

መጽሐፍ ቅዱስ

ሥርዓተ ቤተክርስቲያን